# የመርሃ ግብር መመሪያ (ፖሊሲ)

የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ
BOARD OF EDUCATION OF MONTGOMERY COUNTY

**ተዛማጅ ርእሶች:-** ACD, ACF, ACH, ACH-RA, ACG, BMA, GAA, GBA-RA, GBH, GEG-RA, JHF, JHF-RA

**ኃላፊነት ያላቸው ጽ/ቤቶች:-** Chief of Staff Montgomery County Public School; Teaching, Learning, and Schools; Strategic Initiatives; Districtwide Services and Supports; Human Resources and Development; General Counsel

## አለማዳላት፣ ፍትህ፣ እና የብቃት ባህል

**A. ዓላማ**

የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ በአምስት ዋና ዋና እሴቶች (ትምህርት፣ ግንኙነት፣ አክብሮት፣ ልቀት እና ፍትሃዊነት) የሚመራ የትምህርት ማህበረሰብ ለመፍጠር ያለውን መሻት ለማረጋገጥ።

ለእያንዳንዱ ተማሪ በእኩልነት ለትምህርታዊ ስኬት የሚያበቃ እና አካላዊ፣ ሥነ ልቦናዊ እና ማህበራዊ/ስሜታዊ ደህንነትን ለማዳበር የተነደፉ የትምህርት ዕድሎችን ለመስጠት፡- በጥንቃቄና ለዝርዝሮች ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት የተዘጋጁ ሪሶርሶችን እና ድጋፎችን በፍትሃዊነት ተደራሽነትን በሚያረጋግጥ ሁኔታ ለመስጠት ቦርዱ ያለውን ጥልቅ ቁርጠኝነት ለማረጋገጥ ሲባል ሁሉም ሰራተኞች ምርጥ ሙያዊ ሥራ እንዲሰሩ ኃላፊነት ተጥሎባቸዋል።

የቦርዱ እምነት እያንዳንዱ ተማሪ አስፈላጊ እንደሆነ ማረጋገጥ፣ የእያንዳንዱ ተማሪ ግለሰባዊ ባህሪ ዋጋ ያለው መሆኑንና፣ በተለይም የትምህርት ውጤት በማንኛውም ግለሰብ ተጨባጭ ወይም በግምታዊ የግል ባህሪ መተንበይ እንደሌለበት፤ እና በተማሪዎች ስኬት ጎልተው የሚታዩ ክፍተቶችን በሙሉ ለማስወገድና ፍትኃዊነትን ለማስፈን ከፍተኛ ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል።

ሁሉም ተማሪዎች አለም አቀፍ አስተሳሰብ ባለው ማህበረሰብ ውስጥ እንዲኖሩ እና እንዲሰሩ የሚያዘጋጅ ማዕቀፍ ለመመስረት እና ለማስተዋወቅ፣ ሁሉንም ልዩ እና ግለሰባዊ ልዩነቶች የሚያካትት አዎንታዊ የመማሪያ አካባቢን ለማዳበር፣ እና በኤኮኖሚ ዝቅተኛ የተማሪ ቡድኖች ላይ ስትራቴጂያዊ ትኩረት በመስጠት ማንኛውም የተማሪ ቡድኖች ላይ የማንኛውንም የፕሮግራም፣ የአሠራር፣ የውሳኔ ወይም የድርጊት ተፅእኖ ከግምት ውስጥ ለማስገባት የእኩልነትን ሌንስ መጠቀም ይጠቀማል።

የቦርዱን የማያወላውል ቁርጠኝነት እና አቋም፤ ሁሉም ሰራተኛ ባህላዊ ብቃት ኖሮት/ኖሯት፣ እናም ማንኛውንም ግለሰብ ያለበ(ባ)ትን ሁኔታ ወይም የሚገመት የግል ባህርይ የፈለገውንም ቢሆን እርስበርስ መከባበርን የተካኑ እንዲሆኑ ማረጋገጥ ነው።

የቦርዱን ዋነኛ እሴቶች ለመደገፍ፣ እናም ሁሉንም የፌደራል፣ የስቴት፣ እና የአካባቢ ፀረ-መድልዎ ህጎች መከበራቸውን ማረጋገጥ።

**B. ጉዳይ**

አድልዎ በማንኛቸውም መልኩ አይፈቀድም/ችላ አይባልም። የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ለእያንዳንዱ/ለሁሉም ተማሪዎች እና ሠራተኞች የፈጠራ፣ ማስፋፋት፣ ፍትሕን ማዳበር፣ አብሮነት፣ እና ሁሉን የማቀፍ/የመቀበል ትጋት እና ልማድ እንዲሰፍን የማድረግ የረዥም ጊዜ ጥረቶቹን ይገድባል/ይከለክላል።

ሚዛናዊነት-ፍትኃዊነት በህግ ከተጻፉ ቃላት ባሻገር እንደሚሄድ ቦርዱ ይገነዘባል። ሚዛናዊነት/ትክክለኛ ፍትሕ፥ የወደፊቱን አስቀድሞ ማለምና ከወዲሁ ለማስተካከል/ለማረም ይፋ ያልተገለጹ አሉታዊ አዝማሚያዎችን፣ እና በየተቋሞቹ አብዛኛውን ጊዜ በተወሰኑ ተማሪዎች እና ሠራተኞች ላይ የተተኮረና ያልተመጣጠነ መዋቅራዊ መሰናክሎችን፣ ቁልፍ የሆኑ የትምህርት ፕሮግራሞች እና የስራ መስኮች ላይ ለመሳተፍ እንዳይችሉ የሚደረግባቸውን ማእቀቦች፣ በተማሪ ዲስፕሊን ረገድም የማይገቡ እርምጃዎችን ማረም/መከላከል ይጠይቃል። እርግጠኛ በሆኑ ወይም በግምታዊ የግል ባህርያት ምክንያት ተማሪዎችና ሰራተኞች የሚደርሱባቸውን የታወቁ ኢፍትሃዊ ተፅእኖዎች ለመከላከል/ለማስቆም ሁልጊዜም በንቃት መጠበቅ ያስፈልጋል።

ለዚህ መመርያ ዓላማ፥ ቀጥሎ ያለው ፍቺ-ትርጉም አገልግሎት ላይ ይውላል፡-

1. የዳበረ የብቃት ባህል ማለት ለተለያዩ ባህላዊ መገለጫዎች አድናቆትና አክብሮት መስጠት፣ የራስን ባህል ግንዛቤ ማዳበር፣ እንዲሁም የሌሎችን ባህሎች ማወቅ ምንጊዜም ቀጣይ ሂደት ነው። እናም በድርጅት መስተጋብሮች ውስጥ የሚኖሩ ማህበረሰቦችን ብዙ ባህሎች ለድርጅቱ ጠቃሚ አስተዋፅኦ እንደሚሰጡ ማጠናከር እና ማበልፀግ።

2. መድሎ/ማበላለጥ የሚያካትተው፡- በጥላቻና ቅናት ላይ የተመሰረተ በግለሰቦች ትክክለኛ ወይም ግምታዊ ባህርይ ላይ በመመርኮዝ የሚካሄዱ የጥላቻ ድርጊቶች፤ ረብሻ፣ ግዴለሽነት፣ ማንቋሸሽ፣ ማዋረድ፣ ብቀላ፣ የቃላት ስድብ፣ ንዝንዝ፣ ወከባ፣ ማስፈራራት፣ ሁከት፣ ብጥብጥ፣ ዘለፋ፣ማራከስ/ማጥላላት፣ በጉልበት መደባደብ፣ ዝርፊያ፣ ወይም የትምህርት አካባቢ እና የስራ ሂደትን በሚያደናቅፍ ሁኔታ ንብረት ማበላሸት/ማውደም መድልዎ በተጨማሪም ፊት ለፊት የማይገለጹ ነገር ግን በግለሰቦች ትክክለኛ ወይም በግለሰባዊ ሁኔታዎች ላይ በመመስረት ተገቢ ያልሆነ ተፅእኖ ያላቸው ድርጊቶች ወይም ልምዶችን ያጠቃልላል። አድልዎ ዘረኝነትን፣ ፆተዊ ትምክህተኛነት፣ እና ድርጅታዊ ስር የሰደዱ አግባብነት የሌላቸው ጥላቻዎችን ከሞላ መገለጫዎቻቸው ጋር ያካትታል።

3. ፍትኃዊነት/ሚዛናዊነት፡- እያንዳንዱ ተማሪ እና ሠራተኛ ካለበት ሁኔታ ወይም በይሆናል ግምት ላይ ያልተመሰረተ ግላዊ ተግዳሮቶችም ቢኖሩ፣ በብርታት መሠረታዊ ነገሮችን በማሟላት ለአካደሚክ እና ለሥራ ዝግጁነት ብቁ እንዲሆኑ ለመደገፍ/ለማገዝ እና ለማበረታታት በተግባር የሚረጋገጥ/የሚገለጽ ቁርጠኝነት ነው።

4. ፍትሃዊ እይታ(መነፅር) ማለት ማንኛውም ፕሮግራም፣ ተሞክሮ፣ ውሳኔ ወይም ድርጊት በተለይም በዝቅተኛ ሁኔታ ላይ በሚገኙ የተማሪዎች ቡድን ላይ የሚያሳድረውን ተጽዕኖ ስልታዊ ትኩረት በማድረግ መፍትሔ መስጠት ነው።

5. ውስጠ ታዋቂ አድልዎ (Implicit bias)፡- በግንዛቤአችን፣ ትግባሬአችን፣ እና በውሳኔዎቻችን ላይ ተፅእኖ የሚያደርጉ የተዛቡ አመለካከቶች፣ አቋሞችና ውሱን ባህርያትን ያመለክታል። እነዚህ ከሌላው የበለጠ ለአንድ ወገን የማዳላት አዝማሚያዎች፣ አወንታዊ እና አሉታዊ ግምገማዎችን የሚያካትቱ ሲሆን፥ ሳይታሰብ ወይም ግለሰቡ ሳይታወቀው/ግለሰቧ ሳይታወቃት ወይም ሆን ተብሎ ከቁጥጥር ውጭ በመሆን ሊደረግ ይችላል።

6. የግል ባህሪዎች ዘር፣ ጎሳ፣ ቀለም፣ የዘር ሐረግ፣ ብሔራዊ አመጣጥ፣ ዜግነት፣ ሃይማኖት፣ የስደት ሁኔታ፣ ጾታ፣ የጾታ ማንነት፣ የሥርዓተ-ፆታ መገለጫ፣ የጾታ ዝንባሌ፣ የቤተሰብ/የወላጅነት ሁኔታ፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ ዕድሜ፣ ችሎታ፣ እውቀት (ኮግኒቲቭ)፣ ማህበራዊ/ስሜታዊ፣ እና አካላዊ ሁኔታ፣ ድህነት እና ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ፣ ቋንቋ፣ በሕጋዊ ወይም በሕገ -መንግሥት የተጠበቁ ባህሪዎችን ወይም ግንኙነቶችን ያጠቃልላል።

C. አቋም

1. ቦርዱ፦ ዲስትሪክቱ ለሁሉም ተማሪዎች እና ለሠራተኞች ክንውን ከፍተኛ ተቀባይነት ያለው ሚዛናዊ፣ ፍትሃዊ፣ ደህንነቱ የተጠበቀ፣ ብዝሃነትን (ሁሉን) ያካተተ የአሠራር ባህል ያለበት የሥራ አካባቢ በማዳበር፥ እና የእድሎችን አለመመጣጠን በማስወገድ፣ ለሁሉም ተማሪዎች የስኬት ደረጃን ከፍ እንዲያደርጉ እና የስኬት ክፍተቶችን በከፍተኛ ሁኔታ እንዲሻሻሉ/እንዲስተካከሉ ይጠብቃል።

2. ቦርዱ ጥላቻን የሚያራምዱ ቋንቋን እና/ወይም ምስሎችን እንዲሁም ምልክቶችን መጠቀምን ይከለክላል፥ በተለይም በትምህርት ቤት ወይም በዲስትሪክት ሥራ ወይም እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ማደናቀፍ ሊያስከትል የሚችል ድርጊት-እንቅስቃሴ የተከለከለ ነው። ሆኖም የእንደዚህ ዓይነቶቹ የቃላትና የቋንቋዎች ክልከላ ኃላፊነት ለተሞላበት ውይይት፣ ምስሎች ወይም ምልክቶችን ለትምህርት ዓላማዎች እንዳይውል በመከላከል ጥቅም ላይ አይውልም።

3. ቦርዱ የሚጠብቀው፤ ሁሉም ተማሪዎችና ሰራተኞች የግለሰብ ሁኔታን ወይም ግምታዊ የግል ባህርያትን ሳይመለከቱ እርስበርስ በመከባበር ራሳቸውን በስነስርአት እንዲገዙ ነው።

4. ቦርዱ በትክክለኛ ወይም በግምታዊ የግል ባህርይ ምክንያት በግለሰቦች፣ በተማሪዎችና በሰራተኞች የሚፈፀም፣ ማንኛውንም አይነት አድልዎ ይከለክላል/አይፈቀድም።

5. ቦርዱ በዚህ ፖሊሲ ላይ የሚጠበቀው ሁሉም የቦርድና የ MCPS ሪፖርቶች አቀራረብ እና የውሳኔ አሰጣጥ የዚህን መመርያ ሚዛናዊነት ውጤት ታሳቢ እንደሚያደርጉና ይህ መመሪያ እንደ ሞዴል እንዲያገለግል ወስኗል።

6. በተጨማሪም ቦርዱ የሚከተሉትን ሁኔታዎች ያበረታታል እናም ያራምዳል፦

   a) በሠራተኞች፣ በተማሪዎች፣ በወላጆች/አሳዳጊዎች፣ እና በማህበረሰቡ መካከል ትብብር

      (1) ሰራተኞች ከተማሪዎች ጋር፣ ከወላጆች/ከአስዳጊዎች ጋር፣ እና ከማህበረሰብ አባላት ጋር አብረው በመስራት እያንዳንዱ ት/ቤትና የስራ ቦታ ከአድልዎ ነፃ መሆኑን ማረጋገጥ ይጠበቅባቸዋል።

      (2) ወላጆች/አሳዳጊዎች ለልጆቻቸው በህግ የተቀመጡና በዚህ ፖሊሲ-መመሪያ ላይ የተንፀባረቁ እምነቶች፣ ሃሳቦች፣ እና ግዴታዎች የሚተገበሩ እና የፀኑ እንደሆነ ልጆቻቸውን እንዲያበረታቱ እና ፅኑ እምነት እንዲመሰርቱ እናደፋፍራለን፣ ከዚህ በላይ የተገለጹትን/የሚጠበቁትን ለማሟላት ከ MCPS ሰራተኞች ጋር እንዲተባበሩ እናበረታታቸዋለን።

      (3) ሰራተኞች ትክክለኛም ይሁን ወይም ግምታዊ ግላዊ ባህሪያትን ሰበብ ሳያደርጉ ሁሉንም ወላጆች/አሳዳጊዎች በልጆቻቸው ትምህርት እና ስራ ተሳትፎ እንዲኖራቸውና ተግባራዊ ተሳትፏቸውን የሚያደናቅፉ መሰናክሎችን ለማስወገድ እንዲሰሩ ይጠበቅባቸዋል።

      (4) MCPS በሥራ ግብረኃይል፣ በኮሚቴዎች፣ ሀላፊነት ተሰጥቷቸው የሚሰሩ (ኮሚሽን)፣ እና የልዩ ልዩ ማህበረሰቦችን፣ ባህል፣ ቋንቋዎች፣ እና አመለካከቶችን የሚወክሉ የሌሎችንም አማካሪ አባላትን ጉልህ ተሳትፎ ይፈልጋል።

   b) የትምህርት ዕድሎች እኩልነት

      ቦርዱ የሚከተሉትን ጨምሮ ለሁሉም ተማሪዎች ስኬት ወሳኝ በሆኑ ሁኔታዎች ውስጥ የሚከሰቱ ልዩነቶችን መፍትሔ ለመስጠት ቁርጠኛ ነው።

(a) ከቀለም ትምህርት በተጨማሪ የሚካሄዱ እንቅስቃሴዎችን ጨምሮ ያሉት ሪሶርሶች/መገልገያዎች፣ ጠንካራ ትምህርቶች፣ የፈጠራ ኮርሶች፣ እና ፕሮግራሞች፣

(b) ውጤታማና ብቃት ያላቸው መምህራን፣ መሪዎች፣ እና የድጋፍ ሰራተኞች፣

(c) በቂ መገልገያዎችና መሳሪያዎች፣

(d) ወቅታዊ ቴክኖሎጂ፣

(e) ጥራት ያለው የትምህርት ቁሳቁስ፣

(f) ሚዛናዊ እና ተገቢ የሆነ ትምህርት የሚሰጡ እና ለማንኛውም ተማሪ የትምህርት ዕድሎችን ለማግኘት እንቅፋቶች አለመኖራቸውን የሚያረጋግጡ ተሞክሮዎች እና ሂደቶች፣ እና

(g) በቂ የባጀት ገንዘብ ድጋፍ።

ይህ ቃል መግባት ቀጣይነት የሚኖረውና፣ የበለጠ ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ተጨማሪ ባጀት-ገንዘብ ለማሟላት የታሰበበት ስልት፣ እንዲሁም በይበልጥ ችግር ያላቸው በርካታ ተማሪዎችን ለሚያገልግሉ ት/ቤቶች ሪሶርሶች (resources) እንዴት እንደሚመደቡ የሚያረጋገጥ ነው።

(2) በ MCPS መዋቅራዊ እና በተቋማት ውስጥ ያሉ በሁሉም ት/ቤቶች ተማሪዎች በእኩልነት/በሚዛናዊነት የትምህርት እድሎችን እንዳያገኙ የሚከለክሉ እንቅፋቶችን/መሰናክሎችን ለይቶ ለማወቅና ችግሮቹን ለማስወገድ ይሰራል።

(3) MCPS የዲሲፕሊን ውጤቶች ሚዛናዊ/ፍትሃዊና ትክክለኛ አስተዳደራዊ ይዘት አንድ አካል/ግብአት በመሆኑ በት/ቤቶች ትክክለኛ የትምህርት እድሎችን ለማግኘት ተገቢ እንደሚሆን ይጠበቃል።

(4) የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) መጪዎቹን የብዝሃ ቋንቋ ባለቤቶች የሆኑ የእንግሊዝኛ ተማሪዎችን፥ በትምህርት ቤት፣ በኮሌጅ፣ እና በሥራዎቻቸው የማያቋርጥ እድገት እያሳዩ ከፍተኛ ደረጃ ላይ እንዲደርሱና እንደ ዓለም አቀፍ ዜጎች ሆነው እንዲያስቡ፥ የመጀመሪያ ቋንቋዎቻቸውንና ባህሎቻቸውን እሴት በመጠቀም የማህበራዊ እና አካዳሚክ እንግሊዝኛን/ቋንቋ ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ ይሠራል። MCPS፣ እርግጠኛ ወይም ግምታዊ የሆኑ የግል ባህርያትን ምክንያት ሳይደረግ፣ በት/ቤቶች መካከልና በተመሳሳይ ት/ቤት ውስጥ በሚገኙ ተማሪዎች መካከል በሁለቱም ከበድ ያለ የኮርስ ስራ እና ተመጣጣኝ አካዴሚያዊ ፕሮግራሞች እኩል ያቀርባል።

(5) MCPS፣ በታሪክ ተያይዘው የመጡ ገደቦች ወይም ወግአጥባቂ አስተሳሰቦች ሳይገድቡት፣ ሁሉም ተማሪዎች ግቦቻቸውንና ፍላጎቶቻቸውን እንዲያከናውኑ ያበረታታል። ተማሪዎች በርካታ ከፍተኛ ተፎካካሪነት በሚገጥማቸው ፕሮግራሞች ላይ ለመግባት እና፣ ልዩ ልዩ የት/ቤት እንቅስቃሴዎች፣ አትሌቲክስን ጨምሮ፣ ከስርአተትምህርት-ውጭና አካዴሚያዊ ባልሆኑ ፕሮግራሞች፣ አመለካከታቸውን ለማበልጸግ እና ለትርጉም-አዘልና አርኪ ስራ በመረጡት ስራ ለመሳተፍ የተለያዩ በርካታ እድሎች ይሰጣቸዋል።

(6) MCPS ትምህርት ቤቶችን፣ የመማሪያ ክፍሎችን፣ የሥራ ቦታዎችን እና በት/ቤት ስፖንሰር የሚደረጉ አውደርእዮች (ማስኮቶችን፣ አርማዎችን፣ የቡድን ስሞችን፣ ዜማዎችን፣ ወይም የሙዚቃ ተጓዳኞችን ጨምሮ) ሁሉን የሚያካትት፣ ወደ አንድ ወገን የማያደላ፣ ለሁሉም ምቹና ተስማሚ ሁኔታ እንዲሆን ያበረታታል።

(7) የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ብዝሃነት በሰፈነበት ማህበረሰባችን ውስጥ ከቅድመ መዋእለ ህፃናት እስከ 12ኛ ክፍል ፍትሃዊነትን፣ መከባበርን እና ጨዋነትን የሚያስተዋውቅ፣ የአለምአቀፍ ማህበረሰባችንን ልዩ አስተዋፅኦ በትክክል የሚገልፅ እና የሚወክል ባህላዊ ምላሽ ያለው ሥርዓተ-ትምህርት ይሰጣል፣ እንዲሁም በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት እና ፕሮግራም ውስጥ የብቃት ባህልን ለመቅረፅ ለሠራተኞች እና ለተማሪዎች ዕድል ይሰጣል። ሥርዓተ ትምህርቱ ሠራተኞች የሚከተሉትን አመለካከቶች፣ ክህሎቶች እና ባህሪዎች በመቅረፅ ተማሪዎች እንዲያዳብሩት ያስችላቸዋል፡-

(a) የራስን ቅርስ ዋጋ በመስጠት የሌሎችንም ቅርስ ማክበርና ዋጋ መስጠት;

(b) መከባበር፣ ዋጋ መስጠት፣ እና ልዩነቶችን ማክበር ጤናማ እና በማህበረሰብ ውስጥ ሊያብብና ሊዳብር የሚገባ አስፈላጊ ግብአት ነው።

(c) ለባህላዊ ብዙሃነት መዳበርና ለአብሮነት ዋጋ መስጠት፤

(d) የአብሮነት ግንኙነቶችን ማዳበርና ሕብረ- ባህላዊ አካባቢዎች ላይ በውጤታማነት መስራት፤ እና

(e) ሰዎች በግለሰቦች ሁኔታ ወይም ግምታዊ ባህርይ ምክንያት በሌሎች ላይ ያላቸውን ወግአጥባቂ/ጅምላ አመለካከትን መቋቋም እና ማስወገድ።

(8) በ MCPS ትምህርት ቤቶች ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ የማስተማሪያ ቁሳቁሶች የዓለም ማህበረሰብን ብዝሃነትና ልዩነት፣ ጠንካራ ፍላጎቶችና ምኞቶችን፣ ወሳኝ ጉዳዮችን እና የሴቶች ስኬታማነትን፣ የአካል ጉዳተኝነት ያላቸው ሰዎችን፣ ከተለያዩ ዘር፣ ጎሳ እና ባህል የመጡ ሰዎችን፣ እንዲሁም የተለያየ የፆታ ማንነት ያላቸውን ሰዎች፣ የጾታ መግለጫን፣ ወይም ጾታዊ ዝንባሌን ያንፀባርቃሉ።

c) ዲስትሪክት አቀፍ የዳበረ የብቃት ባህልን ለማሳካት ሙያዊ እውቀት እና ትምህርት

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በሠራተኞች፣ በወላጆች/አሳዳጊዎች እና በማህበረሰብ አባላት መካከል የብቃት ባህልን ለማሳደግ፣ የዲስትሪክት አቀፍ ተሳትፎን ለማበረታታ፣ ልዩነቶችን፣ አለመግባባቶችን እና መፍትሄዎችን ግንዛቤ በማዳበር ውጤታማ ትብብርን ያበረታታል።

d) የሥራ ዕድሎች ሚዛናዊነት/ፍትኃዊነት

(1) የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ብዝሃነትን ያካተተ የሥራ ግብረ ሃይል መፍጠር እና በሁሉም የሰራተኛ አቀጣጠር ስራዎች ሆን ተብሎ ከሚደረግ ወገንተኝነትና አድልዎ ነፃ የሆነ ዲስትሪክት ለመፍጠር ቁጥጥር እና ተገቢ እርምጃ መውሰድ ይቀጥላል።

(2) የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ብዝሃነት የሰፈነበት የሥራ ግብረ ሃይል በመመልመል፣ በመቅጠር፣ እና በማዳበር ረገድ የሚደቀኑ መዋቅራዊና ተቋማዊ መሰናክሎችን ለማስወገድ አወንታዊ እርምጃዎች ይወስዳል።

(3) የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የብዝሃነት ልዩነት ያላቸው ግለሰቦች ባነሰ ተወክለው የሚታዩባቸውን የስራ መስኮች በመለየት፥ በድርድር ስምምነቶቹ መሠረት ብቃት ያላቸውን እጩዎች በቀጣይነት በመመልመል ብዝሃነት የሰፈነበት የሥራ ግብረ ሃይል ያሳድጋል። ለምሳሌ፡- የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ

(MCPS) በፆታቸው ምክንያት በተለምዶ የማይፈቀድላቸው ቦታዎች ላይ መመልመልና ቦታ ማስያዝ ይቀጥላል።

(4) በዚህ ፖሊሲ ውስጥ የተገለጹትን የቦርድ ዋና እሴቶች እና እምነቶችን ከባልንጀራዎች፣ ተማሪዎች፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች፣ እና ከማህበረሰቡ አባላት ጋር በየቀኑ በሚደረጉ መስተጋብሮች ላይ ለማስተጋባት MCPS ሰራተኞችን ያበረታታል።

## D. ተፈላጊ ውጤቶች

1. እያንዳንዱ ት/ቤት እና የሥራ ጣቢያ በቦርዱ መሠረታዊ እሴቶች/እምነት ላይ የተመሰረተ መግባባት፣ መከባበር፣ ትሕትና፣ መቀባበል፣ እና በሁሉም ግለሰብ እና ቡድኖች ዘንድ መልካም ግንኙነትና የመከባበር ባህልን መተግበር ይጠበቅበታል።

2. የትምህርት እና በእኩልነት ስራ የመቀጠር እድሎችን የሚገድቡ መዋቅራዊና ድርጅታዊ ተፅእኖዎች ይወገዳሉ።

3. የ MCPS ትምህርት ቤቶች እና የሥራ ጣቢያዎች ፍትሃዊ፣ ደህንነቱ የተጠበቀና ሠላማዊ፣ ልዩ ልዩ፣ ሁሉን ያካተተ እና ከአድልዎ፣ ከጥላቻ፣ ከጥቃት፣ ከስሜታዊነት እና ያለማክበር ድርጊቶች ነፃ ይሆናሉ።

4. የትምህርት ውጤቶች በሃቀኛ ወይም በተገመቱ ግላዊ ጠባዮች የሚተነበዩ አይሆኑም፣ የተማሪ የፈጠራ ግኝት ክፍተቶችም በሚያመረቃ ሁኔታ ይቀንሳሉ።

5. የ MCPS ተማሪዎች እና ሠራተኞች በሕብረተሰቡ መካከል ትሕትናን፣ መቀባበልን፣ መከባበርን፣ እና መልካም ግንኙነትን በማስተጋባት ጥሩ ተምሳሌትነት ይኖራቸዋል።

6. የሁሉም ተማሪዎች የትምህርት ተሞክሮዎች የማህበረሰቡን ብዙሃዊነት ባህርይ በማንፀባረቅ ይበለፅጋሉ ብዙሃዊነትን ከሚያንፀባርቁ ወገኖች በመጡ ሰራተኞች አማካኝነት፤ ብዙህነትን ግንዛቤ ለሚያራምድ ትምህርት ሁኔታዎችን ማመቻቸት እና በትምህርት ሁኔታ/አቀማመጥ ውስጥ ለሚፈጠሩ የሃሳብ ልውውጦች ጥራት አስተዋፅኦ ያደርጋሉ።

## E. የአተገባበር ስልቶች

1. ቦርዱ እጅግ በጣም ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎችና፣ እንዲሁም ብዙ አስፈላጊ ሪሶርስ የተጓደለባቸውን ተማሪዎች ለሚያገለግሉ ትምህርት ቤቶች ተጨማሪ የባጀት ገንዘብ ድጋፍ በማድረግ ለተማሪዎች ስኬት ወሳኝ የሆኑ ሪሶርሶች ተደራሽነትን የማስፋት ስትራቴጂን በመተግበር በስኬታማነት አንጻር የሚታዩትን የልዩነት ደረጃዎች ያስወግዳል። እና ለሁሉም ተማሪዎች ብቃት ያላቸውና ውጤታማ የሆኑ አመራሮች እና መምህራን በሚዛናዊነትና በፍትሃዊነት መመደባቸውን ያረጋግጣል።

2. MCPS የዚህን መመርያ ሀሳቦች በምሳሌነት ባህል ለመገንባትና ለማስፋፋት ከሰራተኞች፣ ከተማሪዎች፣ ከወላጆች/አሳዳጊዎች፣ እና ከማህበረሰቡ በሞላ ጋር አብሮ ይሰራል።

3. MCPS በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት ውስጥ ፍትሃዊ እና የብቃት ባህል ያለው አሠራርን ለመተግበር ግቦችን፣ ዓላማዎችን፣ ስትራቴጂዎችን እና የጊዜ ገደቦችን መረጃ የመተንተን አሠራርን ሂደት ይለያል። የተማሪ ውጤቶችን፣ ተሳትፎን እና የትምህርት ቤትን ድባብ ለመከታተል በርካታ ጠቋሚ መረጃዎች አስፈላጊ ናቸው፤ እና ለተማሪዎች፣ ለት/ቤት እና ለዲስትሪክቱ የሥራ አፈጻጸም ተጠያቂነትን ለማስፈን የተነደፈ ስልት ጥቅም ላይ ይውላል፤ በተማሪዎች ውጤቶች ላይ ያሉትን የተራራቁ ልዩነቶች ለመቀነስ፥ እና የአካዳሚክ ውጤቶች በእውነተኛ ወይም በግምታዊ የግል ባህሪዎች ሊገመቱ የማይችሉ መሆናቸውን በመገምገም በግልፅ ለሕዝብ ሪፖርት ሊደረግ ይችላል።

4. አትሌቲክስ፣ ከመደበኛ ትምህርት ውጭ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች፣ እና ከአካዳሚክ ውጭ የሆኑ ፕሮግራሞችና እንቅስቃሴዎችን ጨምሮ ትምህርታዊ ፕሮግራሞች፣ ሥርዓተ ትምህርቶች፣ የማስተማሪያ ቁሳቁሶች ለሁሉም ተማሪዎች ዕውቀትን፣ ክህሎትን፣ አመለካከቶችን እና የብቃትን ባህል የማዳበር ባህሪያት

እና በካውንቲያችን፣ በስቴት፣ ብሔራዊ እና በዓለማችን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በሚመጣው ልዩነት ውስጥ ተማሪዎቻችን አብረው እንዲኖሩና እንዲሠሩ የሚያስችሉ ባህሪያትን ያጎናጽፋቸዋል።

5. MCPS እንደየዝንባሌያቸው የተዘጋጀ እና የተለየ ሙያዊ ትምህርት ይሰጣል

   a) የብቃት ባህል እና ምላሽ የመስጠት አቅም መገንባት፣

   b) ተማሪን ማዕከል ያደረገ እና የሁሉንም ተማሪዎች ግለሰባዊ እና የተለያዩ ፍላጎቶችን የሚያሟላ የመማሪያ አከባቢ ለመፍጠር ክህሎትና እውቀት ማግኘት፣ እና

   c) በትምህርት ስርዓቱ ውስጥ የፍትሃዊነት መጓደልን እና የተማሪዎችን ስኬት፣ ማህበራዊ-ስሜታዊ የመማር ሁኔታ እና የተማሪዎችን አካላዊ እና ሥነ-ልቦናዊ ጤናን ሊያደናቅፉ የሚችሉ መሰናከሎችን መፍታት።

6. ሁል ጊዜ ሠራተኞች ይነቃቃሉ፥ ይበረታታሉ –

   a) ለመማር እና ለመስራት በአካል እና በስነ-ልቦና ሠላማዊ እና ደህንነታቸው የተጠበቀ ምቹ አከባቢዎች፤

   b) በሁሉም ሠራተኞች፣ ተማሪዎች፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች፣ እና የማህበረሰብ አባላት መካከል አክብሮታዊ፣ እና ስልጡን ንግግሮችን እና መስተጋብሮችን አርአያ ማድረግ እና ማበረታታት፤ እና

   c) ሪሶርሶችን በመጠቀም-ቤተሰቦች በልጆቻቸው ትምህርት ላይ እንዳይሳተፉ የሚከለክሉትን ባህላዊ፣ የቋንቋ፣ የቴክኖሎጂ ወይም የትራንስፖርት ነክ መሰናክሎችን ለማስወገድ ጥረት ማድረግ-

      1. አስተርጓሚዎች፣

      2. የተተረጎሙ ሰነዶች፣ እና

      3. በ MCPS እና በቤተሰቦች መካከል ግንኙነትን ሊያመቻቹ ከሚችሉ ድርጅቶች ጋር መተባበር።

7. እንደዚህ ዓይነት መድሎአዊ አሠራሮችን ለመከላከል፣ መፍትሔ ለመስጠት፣ ለመከታተል እና የተከሰቱ ሁኔታዎችን ለመመርመርና ለመተንተን ልዩ አይነት ስልቶች ተዘጋጅተው ከሚመለከታቸው ጋር በማጋራት መድልዎን ለመከላከል ያገለግላሉ።

8. MCPS አጋሮችን በመለየት ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ሥራ አስፈፃሚ ጋር፣ ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ካውንስል፣ ከአከባቢ የሕግ አስከባሪ ኤጀንሲዎች፣ ከሌሎች የካውንቲ ኤጀንሲዎች፣ ከማኅበረሰባዊ ቡድኖች፣ ከቢዝነስ ድርጅቶች እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ፍትሃዊነትን ለማሳደግ እና በተማሪዎች እና በሠራተኞች ላይ የሚፈጸም አድልዎን ለመቀነስ በትብብር ይሠራል።

9. ይህ የቦርዱ ፀረ-አድልዎ መመርያና መርህ በህትመት የሚዘጋጁ የ MCPS አምዶች እና በ MCPS ድረ-ገጾች ላይ በቀዳሚነት ይካተታሉ። በእንግሊዘኛ የተዘጋጀው የቦርዱ ፀረ-መድልዎ መመርያ ህትመት በ MCPS ተማሪዎችና ወላጆች/አሳዳጊዎች አዘውትረው በሚጠይቋቸው ቋንቋዎች ትርጉሞችና የማስተርጎም አገልግሎቶች ተዘጋጅተው ይቀርባሉ።

10. የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ይህንን ፖሊሲ ተግባራዊ ለማድረግ ተገቢውን የሚመራ ጽ/ቤት በመሰየም ከሌሎች መስሪያ ቤቶችም እንደአስፈላጊነቱ ድጋፍ እየተሰጠ የሚከተሉትን ኃላፊነቶች ይወስዳል።

a) በ MCPS ሁሉም የፌዴራል፣ የስቴት፣ እና የአከባቢ ፀረ-መድሎአዊነት ሕጎች መከበራቸውን እና ለ MSDE ሪፖርት የማድረግ መስፈርቶች መተግበራቸውን መከታተል እና ማረጋገጥ፣

b) በዲስትሪክት ዙሪያ እና በትምህርት ቤቶች ውስጥ የፍትሃዊነት ተሞክሮዎችን ውጤት ለመለካት የግምገማ ዘዴን መለየት፣

c) የአድሎአዊነት ቅሬታዎችን ወድያውኑ ማጣራትና መፍታት፣

d) የአሠራር ስርአቱን ፍትሃዊነት ለማመቻቸት፣ ለመከታተል እና ለመተግበር ኃላፊነት የሚኖረው-የሚኖራት ግለሰብ መሰየም፣

e) በዚህ መመርያ ስር የቦርዱን እሴቶችና የሚጠበቁ ሥርአቶችን ግንዛቤ ከፍ ማድረግ፣

f) በግምገማዎች ወቅት የፍትሃዊነት መነፅር ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ –

1) ሠራተኞች፣ ሥርዓተ ትምህርት፣ ፔዳጎጂ፣ ሙያዊ ትምህርት፣ የማስተማሪያ ቁሳቁሶች እና የግምገማ ዲዛይኖች፣ እና

2) የሁሉም ሠራተኞች ምልመላ፣ አቀጣጠር፣ ቆይታ እና የእድገት አሰጣጥ ሂደቶች፥

g) ስለ ፀረ-አድሎአዊነት፣ ፍትሃዊነት እና ባህላዊ ብቃትን በተመለከተ ሙያዊ ትምህርት መስጠት፣ እና እነዚህን ጽንሰ-ሀሳቦች በሙያ አስደግፎ ተግበራዊ ለማድረግ ሙያዊ የማዳረስ ሥራ መከወን፣ እና

h) ተገቢ ዘገባዎችን መንከባከብ።

11. የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት በዚህ ፖሊሲ ውስጥ የተገለጹትን እሴቶች የሚያፋልሱና የሚጥሱ ባህርያትን የሚፈጽም-የምትፈጽም ሠራተኛን በሚመለከት ተጨማሪ ሥልጠና ላይ እንዲሳተፍ/እንድትሳተፍ ማዘዝ ይችላል። ቀጣይነት ያለው ቸልተኝነትና-ግድየለሽነትን ቦርዱ አይታገስም እና ከ MCPS የሰራተኛ ስነምግባር ደንብ ጋር በማገናዘብ መባረርን ጨምሮ ተጨማሪ የዲስፕሊን እርምጃ ሊያስከትል ይችላል።

F. *ግምገማ እና ሪፖርት*

1. የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት –

a) በአካባቢ ፍትሃዊነት መስፈኑን የእያንዳንዱን ተማሪ ስኬታማነት ሕግ (ESSA) የተጠናከረ ስትራቴጂያዊ ዕቅድ ማረጋገጥ፤

b) አዝማሚያዎችን ለመተንተን እና ክፍተቶችን ለመለየት የተማሪ መረጃን ነጣጥሎ ማየት፣ እና ፍትሃዊ መፍትሄዎችን ለመፍጠርና ለመደገፍ እንዲህ ዓይነቱን መረጃ መጠቀም፥ እና

c) የዚህን ፖሊሲ አፈጻጸም እና የቦርዱን ዋና እሴቶች የሚያሟላ ፍትሃዊ የትምህርት ስርዓት ለመፍጠር በዲስትሪክቱ የተደረጉ ጥረቶች ለህዝብ እና ለቦርዱ በየጊዜው ወቅታዊ መረጃዎችን መስጠት።

2. በትምህርት ቦርድ የፖሊሲ ግምገማ ሂደት መሠረት ይህ ፖሊሲ በየሦስት ዓመቱ ይገመገማል።

***ተዛማጅ ምንጮች፡-*** MCPS Culture of Respect Compact; Student Code of Conduct in MCPS; MCPS Employee Code of Conduct; MCPS Guidelines for Respecting Religious Diversity; MCPS Guidelines for Student Gender Identity; U.S. Constitution U.S.C.), Amendment 14; Title VI of the Civil Rights Act of 1964, 42 U.S.C. § 2000d et seq.[1]; Title VII of the Civil Rights Act of 1964, as amended, 42 U.S.C. § 2000e et seq.; Title IX of the Education Amendments of 1972, 20 U.S.C. § 1681 et seq.; 34 Code of Federal Regulations (CFR), Part 106, 34 CFR Part 100; Individuals with Disabilities Education Act (IDEA), 20 U.S.C. § § 1400-1487; Section 504 of the Rehabilitation Act of 1973, as amended, 29 U.S.C. § 794; Americans with Disabilities Act (ADA), 42 U.S.C. § 12131 et seq.; Section 1981 of the Civil Rights Act of 1866, 42 U.S.C. § 1981; Age Discrimination in Employment Act of 1967, 29 U.S.C. §§ 621-634; Equal Pay Act of 1963, 29 U.S.C. § 206(d); Equal Rights Amendment to the Maryland Constitution's Patient Protection Affordable Care Act, 42 U.S.C. § 18001 et seq.; Maryland Constitution Declaration of Rights (Article 46); Annotated Code of Maryland, State Government Article, Title 20, Human Relations; Annotated Code of Maryland, Education Article 6-104, 7-424.1; Code of Maryland Regulations (COMAR) 13A.05.01; Montgomery County Racial Equity and Social Justice Act Amendments to Montgomery County Code §1A-201, §2-64A, §2-81C, §27-83, §33A-14.

***የፖሊሲው አመጣጥ፡-*** በውሳኔ ቁጥር 595-69 ኖቬምበር 11/1969 ስራ ላይ ዋለ፤ በውሳኔ ቁጥር 16-72 ጃኑወሪ 11/1972 ተሻሽሏል፤ በውሳኔ ቁጥር 536-77 ኦገስት 2/1977 ተሻሽሏል፤ በውሳኔ ቁጥር 240-96 ማርች 25/1996 ተሻሽሏል፤ በውሳኔ ቁጥር 323-96 ሜይ 14/1996 ተሻሽሏል፤ በውሳኔ ቁጥር 249-03 ሜይ 13/2003 ተሻሽሏል፤ በውሳኔ ቁጥር 318-17፣ ጁን 26/2017 የአርትዖቶች ቅጂ ዲሴምበር 11/2019 የተሻሻለው በውሳኔ ቁጥር 321-21 ጁን 29/2021 ትሻሽሏል።

***ማስታወሻ፡-*** Tenets of Board policies ACB, *Nondiscrimination*, ACE, *Gender Equity*, GBA, *Workforce Diversity*, and GMA, *Human Relations Training of MCPS Staff*፥ ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት ደንቦችና መመሪያዎች ቀጥሎ ባለው የውሳኔ ቁጥር ተጠቃለዋል። 318-17 በዚህኛው ፖሊሲ ማሻሻያ ተደርጎ ጁን 26/2017 በፀደቀው የቦርድ ፖሊሲ "Board Policy ACA" ተተክቷዋል።

[1] Culture of Respect Compact/በመከባበር ላይ የተመሰረተ ባህል በ MCPS፣ የሞንጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ማህበር፣ አለም-አቀፍ የአገልግሎት ሰራተኞች ማህበር Local 500፣ እና የሞንጎመሪ ካውንቲ የአስተዳዳርና የርእሰመምህራን ማህበር መካከል የተደረገ ስምምነት፡-